أداء الأمانة

إعداد:
الشيخ زيد بن محمد
بن هادي المدخلي

አደራን መወጣት

ትርጉም፡
ዩሱፍ አሕመድ

http://t.me/alateriqilhaq



እንቲ ሙስሊም ሆይ! ፊትህን ለእርሱ ተገዥ ያደረክለት ፤ የበጎ ነገሮች ፣ የትሩፋቶች ፣ የሲሳይና የመፍጠር ባለቤትነቱን ያረጋገጥክለት አላሁ ﷻ በአቅምህና በችሎታህ መጠን ልትፈጽማቸው የምትችላቸው በርካታ ነገሮችን በአደራ መልክ የጣለብህ መሆኑን እወቅ።

አላህ - ሱብሃነሁ ወተዓላ - በሰጠህ አደራ ለወደፊት ይጠይቅሃል። አደራህን በአግባቡ ከተወጣህ አላህ - ሱብሃነሁ ወተዓላ - በተባረክ ፣ ጸጥታና መረጋጋት በተሞላበት አገር ያኖርሃል። አደራህን በአግባቡ ካልተወጣህ ደግሞ በሓጢያት ፣ በኪሳራ ፣ በጸጸትና በውርደት ትመለሳለህ።

ከተሰጠህ አደራዎች መካከል፡-

(1). በእውነት የሚመለክ አምላክ ከእርሱ በቀር አንድም እንደሌለ ፤ ከእርሱ ውጭ ያለው አምልኮት ሁሉ የውሸት አምልኮት እንደሆነና ሙሐመድ ﷺ የአላህ የመጨረሻ መልክተኛ መሆናቸውን ፤ እርሳቸው ከመጡበት ህግ ውጭ ሰዎች የሚዳኙበት አንድም ትክክለኛ ህግ የሌለ መሆኑን ማረጋገጥና መመስከር ነው።

ከአላህ ውጭ ያሉ አካላት ለአምልኮት ተገቢዎች ናቸው ብሎ የሞገተ ሰው ከትክክለኛው መንገድ ያፈነገጠ ፣ እውነትን በውሸት የቀየረ ፤ ከትክክለኛው መንገድ ይልቅ እውርነትን አማራጭ አድርጎ የያዘ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል።

አላህ በተከበረው ቁርኣን የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿قُلْ يَا أَيُّهَا النَّاسُ إِنِّي رَسُولُ اللهِ إِلَيْكُمْ جَمِيعًا الَّذِي لَهُ مُلْكُ السَّمَاوَاتِ وَالأَرْضِ لا إِلَـهَ إِلاَّ هُوَ يُحْيِي وَيُمِيتُ فَآمِنُواْ بِاللهِ وَرَسُولِهِ النَّبِيِّ الأُمِّيِّ الَّذِي يُؤْمِنُ بِاللهِ وَكَلِمَاتِهِ وَاتَّبِعُوهُ لَعَلَّكُمْ تَهْتَدُونَ﴾

"(ሙሐመድ ሆይ!) በላቸው፡- "እናንተ ሰዎች ሆይ! እኔ ወደናንተ ወደሁላችሁም የአላህ መልክተኛ ነኝ። (እርሱም) ያ የሰማያትና የምድር ንግሥና ከእርሱ ብቻ የሆነ ነው። እርሱ እንጂ ሌላ አምላክ የለም። ሕያው ያደርጋል። ይገድላልም። በአላህ በዚያም በአላህና በቃላቶቹ በሚያምነው የሚይጽፍ የሚያነብ ነቢይ በሆነው መልክተኛው እመኑ። ቅንንም መንገድ ትመሩ ዘንድ ተከተሉት።" *(አል'አዕራፍ ፡ 158)*

(2). በአጠቃላይ በእስልምና ፣ በእምነት እና በበጎ ስራዎች ማዕዘናት አምኖ መስራት አላህ በሰው ልጆች ላይ የጣለው አደራ ነው። ወንድም ይሁን ሴት በእነዚህ ማዕዘናቶች ላይ ቆሞ በእውቀትና በተግባር ወደርሷ ጥሪ ያደረገ በእርግጥም አደራውን የተወጣ እርሱ ነው። ይህን የተሰጠውን አደራ ያጓደለ ከእርሱ ላይ በተከሰተው የማጓደል መጠን በትንሳኤ ቀን ተጠያቂ ይሆናል።

(3). ውስጥንና ውጭን ማጽዳት ፡ ውስጣዊ ጽዳት የሚባለው የዓቂዳ መጣመምን ፣ የስነ-ምግባር መዛባትን ማስተካከል ሲሆን ውጫዊ ጽዳት ደግሞ አላህ በሰጠን ንጹህ ውሃ ውዱእ ከመፍታትና ከነጃሳ መጽዳት ማለት ነው።

አላህ በተከበረው ቁርኣን የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿وَأَنزَلْنَا مِنَ السَّمَاء مَاء طَهُورًا﴾

"ከሰማይም አጥሪን ውሃ አወረድን" *(ኣል'ፉርቃን ፡ 48)*

ውሃ ከጠፋ በመልካም የመሬት ገጽ ላይ በሚገኘው አፈር ተየሙም በማድረግ ንጽህናችንን መጠበቅ ያስፈልጋል።

አላህ በተከበረው ቁርኣን የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُواْ إِذَا قُمْتُمْ إِلَى الصَّلاةِ فاغْسِلُواْ وُجُوهَكُمْ وَأَيْدِيَكُمْ إِلَى الْمَرَافِقِ وَامْسَحُواْ بِرُؤُوسِكُمْ وَأَرْجُلَكُمْ إِلَى الْكَعْبَيْنِ وَإِن كُنتُمْ جُنُبًا فَاطَّهَّرُواْ وَإِن كُنتُم مَّرْضَى أَوْ عَلَى سَفَرٍ أَوْ جَاء أَحَدٌ مِّنكُم مِّنَ الْغَائِطِ أَوْ لاَمَسْتُمُ النِّسَاء فَلَمْ تَجِدُواْ مَاء فَتَيَمَّمُواْ صَعِيدًا طَيِّبًا فَامْسَحُواْ بِوُجُوهِكُمْ وَأَيْدِيكُم مِّنْهُ مَا يُرِيدُ اللّهُ لِيَجْعَلَ عَلَيْكُم مِّنْ حَرَجٍ وَلَـكِن يُرِيدُ لِيُطَهَّرَكُمْ وَلِيُتِمَّ نِعْمَتَهُ عَلَيْكُمْ لَعَلَّكُمْ تَشْكُرُونَ﴾وَاذْكُرُواْ نِعْمَةَ اللّهِ عَلَيْكُمْ وَمِيثَاقَهُ الَّذِي وَاثَقَكُم بِهِ إِذْ قُلْتُمْ سَمِعْنَا وَأَطَعْنَا وَاتَّقُواْ اللّهَ إِنَّ اللّهَ عَلِيمٌ بِذَاتِ الصُّدُورِ﴾

"እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ወደ ሶላት በቆማችሁ (ከመቆም ባሰባችሁ) ጊዜ ፊቶቻችሁን ፣ እጆቻችሁንም እስከ ክርኖች እጠቡ። ራሶቻችሁንም (በውሃ) አብሱ። እግሮቻችሁንም እስከ ቁርጭምጭሚቶች (እጠቡ) ። (ሴት ጋር በመገናኘት ወይም በሌላ ምክንያት ጀናባ ብትሆኑ (ገላችሁን) ታጠቡ። በሽተኞች ወይም በጉዞ ላይ ብትሆኑም ወይም ከእናንተ አንዳችሁ ከዓይነ ምድር ቢመጣ ወይም ሴቶችን ብትነካኩና ውሃን ባታገኙ ንጹህን የምድር ገጽ አስቡ። ከሱም ፊቶቻችሁንና እጆቻችሁን አብሱ።

አላህ በእናንተ ላይ ምንም ችግር ሊያደርግ አይሻም። ግን ታመሰግኑ ዘንድ ሊያጠራችሁና ጸጋውን በእናንተ ላይ ሊሞላ ይሻል። በእናንተም ላይ (የከገሰውን) የአላህን ጸጋ ያንንም ሰምተናል ታዘናልም ባላችሁ ጊዜ በርሱ ያጠበቀባችሁን ቃል ኪዳኑን አስታውሱ ። አላህንም ፍሩ። አላህ በደረቶች (በልቦች) ውስጥ ያለውን ሁሉ አዋቂ ነውና።" *(አል'ማኢዳ፡ 6-7)*

የውስጥ እና የውጭ ንጽህናዎችን በአላህና በረሡል ﷺ ፍላጎት መሰረት ተፈጻሚ ያደረገ የተሰጠውን አደራ በአግባቡ የተወጣ እርሱ ነው። እነርሱን ያጠፋ ወይም ያጓደለ በትንሳኤ ቀን ተስማሚ ዋጋውን አላህ ይከፍለዋል።

(4). አጠቃላይ የሰውነት አካላችን ከአላህ የተሰጠን አደራ ነው። በእያንዳንዷ የሰውነት ብልታችን ምን እንደሰራንበት ለወደፊት እንጠየቃለን ፤

ከሰውነት አካላችን በደንብ ልንጠብቀው የሚገባ ብልታችን ነው። እያንዳንዱ ሰው በብልቱ ሀራም እንዳይሰራ ሊጠነቀቅ ይገባል። ብልቱን በሀራም ከተጠቀመበት የተሰጠውን አደራ ባለመወጣቱ ዱንያዊም ይሁን አኼራዊ ቅጣት ይኖርበታል።

አላህ በተከበረው ቁርኣን የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿الزَّانِيَةُ وَالزَّانِي فَاجْلِدُوا كُلَّ وَاحِدٍ مِّنْهُمَا مِئَةَ جَلْدَةٍ وَلَا تَأْخُذْكُم بِهِمَا رَأْفَةٌ فِي دِينِ اللَّهِ إِن كُنتُمْ تُؤْمِنُونَ بِاللَّهِ وَالْيَوْمِ الْآخِرِ وَلْيَشْهَدْ عَذَابَهُمَا طَائِفَةٌ مِّنَ الْمُؤْمِنِينَ﴾

"ዝሙተኛይቱና ዝሙተኛው ከሁለቱ እያንዳንዳቸውን (ያካገቡ እንደሆኑ) መቶ ግርፋትን ግረፉዋቸው ፤ በእነርሱም በአላህ ፍርድ ርህራሄ አትያዛችሁ። በአላህና በመጨረሻው ቀን የምታምኑ እንደሆናችሁ (አትራሩ) ። ቅጣታቸውንም ከምእምናን ጭፍሮች ይገኙበት።" *(አን'ኑር፡ 2)*

ሙስሊምና ሌሎችም የሐዲስ መዛግብቶች በዘገቡት ዑባዳ ብን ሷሚት ﷺ ከነብዩ ﷺ ሰምተው የሚከተለውን ሐዲስ አስተላልፈዋል፡-

"خذوا عني خذوا عني ، قد جعل الله لهن سبيلا ، البكر بالبكر ، جلد مائة ، ونفي سنة ، والثيب بالثيب ، جلد مائة الرجم" رواه مسلم

"ከእኔ ውሰዱ ፤ ከእኔ ውሰዱ ፤ አላህ ለሴቶች ሃግን አደረገላቸው ፤ አግብቶ የሚያውቅ አግብታ በማታውቅ ላይ (ዝሙት ከሰራ) መቶ መገረፍና አንድ አመት ከአገር መባረር ፤ አግብቶ የሚያውቅ አግብታ በማታውቅ ላይ (ዝመት ከሰራ) መቶ መገረፍና ተወግሮ መገደል።" *(ሙስሊም፡ 1690)*

ከላይ በቁርኣንና በሐዲስ የተጠቀሱት ቅጣቶች ሁሉ ብልትን ባለመጠበቅ የተደነገጉ ናቸው። ስለዚህ በተፈቀደው እንጅ ክልክል በሆነው መጠቀም አይገባም።

መስሚያው ለባለቤቱ የተሰጠ የአላህ አደራ ነው ፤ ጀሮውን አላህ ለሚወደው ነገር እንጅ ለሌላ አገልግሎት ሊያውለው አይገባም። ቁርኣንን ፣ የነብዩን ﷺ ሐዲስ ፣ ኹጥባዎችን ፣ መልካም ተግሳጾችን ፣ ለዲንም ለዱንያም ሊጠቅሙ የሚችሉ ነገሮችን ሊያዳምጥበት ይገባል።

ጀሯችን ክልክል የሆኑ ነገሮችን ሊያዳምጥ አይገባም። ሙስሊሞች ጥቃት እንዲደርስባቸው ለመሰለል፣ ለሀሜት ፣ ወሬን ከአንዱ ወደሌላ ለመውሰድ ፣ ለማጣላት ፣ ውሸት እና ጸያፍ ንግግር ለማዳመጥ ፤ ዘፈንን ለመስማት መዋል የለበትም። ከእነዚህ ነገሮች ሁሉ መጽዳት ግዴታው ነው። መሰንቆ፣ ጃዝ፣ ሳክስፎን ፣ ትራምፔት እና የመሳሰሉትን የሙዚቃ መሳሪያዎች ማዳመጥ የለበትም። የአጅነብይ ሴቶችን ድምጽ መስማት የለበትም። ይህን ካደረገ አላህ የሰጠውን የሰውነት መሳሪያ በአግባቡ አልተጠቀመበትም ፤ የተፈጠረበትንም አላማ እና አላህ የሰጠውን አደራ በአግባቡ አልተወጣም ማለት ነው።

አይን ከአላህ የተሰጠ አደራ ነው። ጥቅም የሚያስገኙ ነገሮችን ለምሳሌ፦ የአላህን ኪታብ ፣ የነብዩን ሱና ፣ በዲንም ይሁን በዱንያ ጠቃሚ የሆኑ ኪታቦችን መመልከት አለበት። የጌታውን ሐያልነት ለመገንዘብ፣ ለማስተንተን እና በእነርሱም ማስረጃ ለማድረግ የአላህን አስገራሚ ፍጡሮች መመልከት በአጠቃላይ ማየቱ የሚበቃ ነገር ሁሉ መመልከት የተፈቀደ ነው። በአጅነብይ ሴቶች እርካታን ለማግኘት አስቦ መመልከት የለበትም። ይህን የሚያደርግ ከሆነ አደራውን አልተወጣም። ይህን የሚፈጽም ከሆነ ትክክለኛ ዓቅል የማያረጋግጠው ፤ አምላካዊ ሸሪዓም የማይወደው ተግባርን ፈጸመ።

ምላስ አላህ አደራ ያስቀመጠበት የሰውነት አካል ነው። በጥቅምም በጉዳትም ከአካል ሁሉ ትልቁ እርሱ ነው። ይህን ትንሽ አካል ከተጠቀመበት ማለትም ሐቅ ለመናገር ፣ ቁርኣን ለመቅራት ፣ የተለያዩ ዚክሮችን ለመዝከር ለምሳሌ፦ ኢስቲግፋር ፣ ለሰዎች የዲናቸውን ጉዳይ ለማስተማር ፤ በመልካም ለማዘዝ ፤ ከመጥፎ ለመከልከል ፤ ለእነርሱ ምክር ለመስጠት እና የመሳሰሉ መልካም ንግግሮችን ለመናገር የሚጠቀምበት ከሆነ በዱንያም በኣኼራም መልካም ፍሬውን ይለቅማል። እንዲሁም አማናውን ወይም አደራውን ጠባቂ ይሆናል።

አላህ ከሰጠው አደራ ውጭ የሚጠቀም ከሆነ ፤ መጥፎ ንግግር የሚናገር፣ የሚዋሽ፣ የሚሳደብ፣ የሚዘልፍ፣ የሚያማ፣ የሚያሾፍ፣ እውነታውን የሚገለብጥ፣ ሐቅን የሚንቅ፣ ባጢልን ለመርዳትና ሐቅን ለመናቅ የሚጠቀምበት ከሆነ አማናውን አልተወጣም። የአካል ክፈሎቹ የተፈጠሩለትን አላማ ስተዋል።

ሆድ አላህ የሰጠን አደራ ነው። ወደሆዳችን ሀላል ወይም የተፈቀደልንን ምግብና መጠጥ ብቻ ማስገባት ይኖርብናል። ሆዳችን የመልካም እንጅ የሀራም ጆንያ መሆን የለበትም። የሀራም አቁማዳ ካደረገው በእርግጥ የተፈጠረለትን አላማ ስቷል ፤ በዚህ ሰውነቱ አማናውን አልተወጣም።

እጅም እግርም አላህ የሰጠን አደራ ነው። በመሆኑም በዱንያም ይሁን በአኼራ ጥቅም የሚያስገኙ ነገሮችን ለማምጣት መጥፎ ነገሮችን ደግሞ ለመከላከል መጠቀም አለብን። ሲንቀሳቀስም ይሁን ሳይንቀሳቀስ የአላህን ህግጋት ከተጠባበቀ አደራውን ተወጥቷል። እግርና እጁን በማይፈቀዱ ነገሮች ላይ ከሸማቸው ለምሳሌ የንጹሐንን ደም ለማፍሰስ፣ ሰዎችን ለመደብደብ ፣ ገንዘብ ለመዝረፍ የሚጠቀምባቸው ከሆነ አደራውን አልተወጣም። እነዚህ አካላቶች ከአላህ የሆኑ ጸጋዎች መሆናቸውን ለወደፊት የሚጠየቅባቸው መሆኑንም ማወቅ ይኖርበታል።

አላህ በተከበረው ቁርኣን የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿وَلاَ تَقْفُ مَا لَيْسَ لَكَ بِهِ عِلْمٌ إِنَّ السَّمْعَ وَالْبَصَرَ وَالْفُؤَادَ كُلُّ أُولـئِكَ كَانَ عَنْهُ مَسْؤُولاً﴾

“ከአንተም በእርሱ ዕውቀት የሌለህን ነገር አትከተል። መስሚያ ፣ ሚያም ፣ ልብም እነዚህ ሁሉ (ባለቤታቸው) ከእነሱ ተጠያቂ ነውና።” *(አል’ኢስራእ፡ 36)*

ሌላው ሀላፊነት ልጆችን ከትኩቶ የማሳደግ ሐላፊነት ነው። ለሚያስተዳድራቸው ምክርን መለገስ ፤ ወደአላህ ጥሪ ማድረግ ፤ የቅርብ ዘመዶችን እና የጎረቤቶቹን ሐቅ መወጣት ፤ ከእነርሱ ጋር የተያያዙ ስራዎችን ሁሉ አላህን ፈርተን ተፈጻሚ ማድረግ ፤ በማንኛውም የስራ አይነት ማገዝ ናቸው።

በዚህ ባቀረብነው የአማና ዝርዝር አንድ የተከበረ አንባቢ ምን ያክል ሀላፊነት እንዳለበት በደንብ ይገነዘባል ፤ የአማናን አንገብጋቢነት ያውቃል ፤ በተወረደው የአላህ ሸሪዓ እርሷን በመጠበቅ እድለኛ ህይዎት ያገኛል። እርሷን በማጥፋት ወይም በማጉደል የህይዎት ሚዛን ይጓደላል። ፍጻሜው ይከፋል ፤ መበታተን ይሰፍናል ፤ ያለምንም ስጋት ያለምንም ትህትና ያለማስተንተን የመጨረሻውን ሁኔታ ያለማስተዋል ጠንካራው በደካማው ላይ ጫና ይፈጥራል።

أداء الأمانة

إعداد:
الشيخ زيد بن محمد
بن هادي المدخلي

አደራን መወጣት

ትርጉም፡
ዩሱፍ አሕመድ



ባህር ዳር በሚገኙ የአህለሱና መሻይኾች የተቀሩ ጠቃሚ ኪታቦች፣ ከሀገር ውስጥና ከውጭ በሚመጡ መሻይኾች የተሰጡ ኮርሶች፣ ሙሐደራዎች፣ የጁመዓ ኹጥባ፣ በትክክለኛ ሚስረጃ የተደገፉ የተለያዩ ኢስላማዊ መጣጥፎችን የሚከተለውን የቴሌግራም ኪንክ ጆይን በማድረግ መከታተል ይችላሉ

http://t.me/alateriqilhaq